QuickNotes mcps

2013-2014 ጎረቤት ከጎረቤት፡- ተሳተፉ!

የMCPS ጎረቤት ከጎረቤት (N2N) ማህበረሰብ አባላትን በአስፈላጊ የት/ቤት ስርአት ርእሶች በአነስተኛ ቡድን ውይይት ለማስተናገድም ሆነ ለመሳተፍ እድል ይሰጣቸዋል። ከኖቬምበር 1 ቀን ጀምሮ፣ በሁለት የተለያዩ የ(N2N) ውይይት የመሳተፍ እድል ይኖራችኋል።

- **የMCPS ስራ ማስኬጃ በጀት፡-** MCPS ማወቅ የሚፈልገው ወላጆችና የማህበረሰብ አባላት ከት/ቤቱ ዲስትሪክት በጀት በሚመጣው አመትና ከዚያ ባሻገር ምን ዋጋ እንደሚሰጡት፤
- **Bell Times (የደወል ግዜዎች)፡-** የበላይ ተቆጣጣሪ ጆሹዋ ስታር ስላቀረበው የትምህርት መጀምርያና መጨረሻ ሰአታት — የደወል ግዜዎች ተብሎ ስለሚታወቀውም — ተማሪዎችና ህብረተሰቡ ላይ ስለሚያስከትለው ትፅእኖ የናንተን አስተያየት ዲስትሪክቱ ማወቅ ይፈልጋል።

የጎረቤት ከጎረቤት ድር ጣብያ ውይይት ለማስተናገድ ወይም ለመሳተፍ ለሚፈልጉ በመገለግያዎች የተሞላ መሳርያ ጥቅል ያቀርባል። እነዚህ ውይይቶች በተለያዩ ግዜያትና ቦታዎች ሊከናወኑ ይችላሉ — በPTA ስብሰባ ከሌሎች ወላጆች ጋር፣ በ"ብራውን ባግ" ምሳ ወቅት ከስራ ባልደረቦች ጋር፣ ወይም በመንደራችሁ በመኖርያ ቤት ከጓደኞች ጋር!

የጎረቤት ከጎረቤት ድርጊት ማስተናገድ ወይም መሳተፍ ትፈልጋላችሁን? ልትወስዷቸው የምትችሉ የተወሰኑ እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

step 1 one

**አንድ ቡድን አሰባስቡና ቦታ ምረጡ;** የN2N ውይይት ለማስተናገድ ሁሉም ተጋብዟል። የቡድኑ ብዛት እንደ አስተናጋጁ ነው፣ ሆኖም ሁሉም የመሳተፍ እድል እንዲኖረው አረጋግጡ። ኢንተርኔት ያለው ቦታ ይመረጣል፣ የተገኙት የመሳርያው ጥቅል አካል የሆኑትን ሰነዶችና ቪድዮዎች ማየት እንዲችሉ። ከመስመር-ውጭ (ከኮምፒውተር ውጭ) የቪድዮ ቅጂ ካስፈለጋችሁ፣ በpio@mcpsmd.org ኢሜይል አድርጉ።

step 2 two

**ቪዲዮ ተመልከቱ ሰነዶችንም አገላብጣችሁ እዩ።** ቪድዮዎቹ የMCPSን በጀት አጠቃላይ ይዘትና የደወል ሰአቶች ረቂቅ ያሳዩዋችኋል። ቪድዮዎቹ፣ ከሰንዶቹ ጋር፣ ለውይይታችሁ መነሻ ይሆናሉ።

step 3 three

**ተወያዩ።** ውይይታችሁን የምትጀምሩበት ሰአቱ አሁን ነው። ውይይቱን ለመጀመር የሚያግዙ መሪ ጥያቄዎች በመሳርያ ጥቅል ውስጥ አሉ። አንድ ሰው ማስታውሻ መያዙን አረጋግጡ፣ ካስፈለገም፣ ከMCPS ማህበረስብ ጋር የምትጋሯቸው የውይይታችሁን ፎቶዎችንም ውሰዱ።

ሃሳቦቻችሁን ተጋሩ። ማስታወሻችሁንና ለማጋራት የምትፈልጓቸውን ፎቶዎች በpio@mcpsmd.org ኢሜይል አድርጉ። በቡድኑ የሚገኘውን ሰው ሁሉ ስም መጻፍ የለባችሁም፣ የአስተናጋጁ/ጇ ስምና መገናኛ መረጃዎች ግን ጠቃሚዎች ይሆናሉ። በN2N ድር ጣብያ የሚገኘውን ኤሌክትሮኒክስ ቅፅ በመሙላት አስተያየቶች መጋራትም ትችላላችሁ። የስራ ማስኬጃ በጀትና የደወል ሰአቶች ለውጥ የመጨረሻ ውሳኔ በሚያደርጉበት ወቅት ሁሉም ማስታወሻዎች ከትምህርት ቦርድና ከበላይ ተቆጣጣሪ ጋር ይጋራሉ።

ስለ ደወል ሰአቶች MCPS የህብረተሰብ ዳሰሳ ጀመረ

በሚቀጥሉት ወራት Montgomery County Public Schools (MCPS) የደውል ሰአቶች ተብለውም በሚጠሩት የትመህርት መጀመርያና መጨረሻ ሰአቶች የቀረቡ ለውጦችን በሚመለከት አስተያየቶች ለመስጠት በርካታ እድሎችን ይሰጣል። የህም የማህበረሰብ መድረኮች፣ የትኩረት ቡድኖችና ዳሰሳዎች/መጠይቆች፣ እና በራስ የሚመራ ጉድዩን ለማጥናትና አስተያየት መስጫ የሆነውን "ጎረቤት ከጎረቤት"ን ያካትታል።

በሁሉም መድረኮች፣ የበላይ ተቆጣጣሪ ጀሹዋ ስታር የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች 50 ደቂቃ ዘግይተው እንዲጀምሩ፣ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከ10 ደቂቃ በኋላ፣ የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች የትምህርት ቀን በ30 ደቂቃ እንዲራዘም ባቀረቡት ረቂቅ ጥያቄዎች ለማቅረብና አስተያየት ለመጋራት እድሎች ይኖሯችኋል።

የመጀመርያው የማህበረሰብ መድረክ ኦክቶበር 28 ይከናወናል። የሌሎቹ ሶስት ማህበራዊ መድረኮች እለቶችና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- **ሰኞ፣ ዲሰምበር 16፡-** Richard Montgomery High School, 250 Richard Montgomery Drive in Rockville
- **ሰኞ፣ ጃኗሪ 6፡-** Seneca Valley High School, 19401 Crystal Rock Drive in Germantown
- **ሰኞ ፈብሩዋሪ 10፡-** Montgomery Blair High School, 51 University Blvd., East, in Silver Spring

ሁሉም መድረኮች የሚከናወኑት ከ7 p.m. –8:30 p.m. ነው። ነፃ የልጆች (4 አመትና ከዚያ በላይ) እንክብካቤና የትርጉም አገልግሎቶች ይኖራሉ።

በቀረበው ረቂቅ አስተያየቶች አንዴ ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ጠቅላላ ዋጋና በስራ እንቅስቃሴ የሚኖሩ ተፅእኖዎችም ከተወሰኑ፣ ዶ/ር ስታር እና የትምህርት ቦርድ ስለ ደወል ሰአቶች የመጨረሻ ውሳኔ በስፕሪንግ መጨረሻ ላይ ይሰጣሉ። እጅግ ፈጠነ ቢባል በመጀመርያና በመጨረሻ ሰአቶች የሆኑ ለውጦች ተግባራዊ የሚሆኑት በ2015-2016 የትምህርት አመት ላይ ነው።

ለተጨማሪ መረጃዎች፣ Bell Times ድር ጣብያ ጎብኙ።

**የወላጆች አካዴሚ ዎርክሾፕ በጠቃሚ ምክሮች ተሞልቷል**

Office of Community Engagement and Partnerships (የማህበረሰብ ተሳትፎና ሽርክና ፅ/ቤት) (OCEP) በኖቨምበር ውስጥ ውጤታማ ልጅ-አሳዳጊነት ችሎታዎች፣ የኮምፒውተር ደህንነትና ህዝባዊ ሚድያ፣ የኮሌጅን ዋጋ መወጣት፣ እና ስልታዊ የፐላን ዝግጅት መዋቅርን የሚያካትቱ በተለያዩ ርእሶች ነፃ የወላጅ አካዴሚ ዎርክሾፖች ያካሂዳል። ኑና ልጆቻችሁን ለመርዳት በምትሳተፉበትና ስልቶችን በምትገነቡበት ዳሰሳ አድርጉና ተወያዩ።

የክፍሎችን ፕሮግራም በሚመለከት፣ [የወላጅ አካዴሚ ድረ ጣብያ] ጎብኙ ወይም OCEPን በ301-279-3100 ደውሉ።

**ዜና ስለ Consortia (ኮንሶርሽያ) እና የማመልከቻ ፕሮግራሞች**

**የመጨረሻ ገደብ ቀን በ*Choice (ምርጫ)* ሂደት ለመሳተፍ እና ለማመልከት-ብቻ ፕሮግራሞች አርብ፣ ኖቨምበር 8 ነው።**

የመጨረሻ ገደብ ቀን በ*Choice (ምርጫ)* ሂደት ለመሳተፍ እና ለማመልከት-ብቻ ፕሮግራሞች አርብ፣ ኖቨምበር 8 ነው። የ*Choice* ፎርሞች በMiddle School Magnet Consortium (MSMC) ለሚኖሩ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችና በDowncounty Consortium (DCC) እና በNortheast Consortium (NEC) ለሚኖሩ የ8ኛ ክፍልተማሪዎች በፖስታ የሚላከው በኦክቶበር አጋማሽ ላይነው። ስለ *Choice* ሂደት ተጨማሪ መረጃ የሚከተሉትን ድር ጣብያዎች ጎብኙ፡-

[NEC]
[DCC]
[MSMC]

ለዲስትሪክቱ አዲስ ከሆናችሁ፣ Division of Consortia Choice and Application Program Services (የኮንሶርሽያ ምርጫ ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎቶች ክፍል) ኖቨምበር 5 ከ5 – 7:30 p.m. የተማሪ ምዝገባ ስብሰባ ያካሂዳል። ይህ ስብሰባ በ2014 በNEC እና DCC የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ወይም በMSMC መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚገቡ አዳዲስ ተማሪዎች ወላጆች ነው። ለተጨማሪ መረጃ፣ 301-592-2040 ደውሉ።

**የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ ስብሰባ ለኖቨምበር 25 ታቅዷል።**

MCPS Special Education Advisory Committee (የMCPS ልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ) ሰኞ፣ ኖቨምበር 25 ከ7 p.m. – 8 p.m. በCarver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive in Rockville አዳራሽ ስብሰባ ያካሂዳል የምሽቱ እንግዳ ተናጋሪ የበላይ ተቆጣጣሪ ጆሹዋ ፒ ስታር ነው። ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች ወላጆች ስብሰባው እንዲገኙና በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ላይ ተፅእኖ ባላቸው ርእሶች እንዲወያዩ ተጋብዘዋል። ለተጨማሪ መረጃ Department of Special Education Services (የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች መምርያ) በ301-279-3135 ተገናኙ።

ወደ ትምህርት ቤት አርበኛ ይዛችሁ ሂዱ ቀን!

ወደ ትምህርት ቤት አርበኛ ይዛችሁ ሂዱ ቀን በHistory Channel (የታሪክ መስመር) የዳበረ አርበኞችን ከተማሪዎች ጋር በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚያገናኝ ብሄራዊ ፕሮግራም ነው። ት/ቤቶችና ማህበረሰቦች ከየአቅጣጫው የሚመጡ አርበኞችን ታሪካቸውን እንዲያጋሩና ስለአገልግሎቶቻቸው ምስጋና እንዲቀበሉ ይጋብዟቸዋል። ይህ ክውነት፣ ወደ ኖቨምበር 11 በሚያመሩት ሳምንቶች የሚደራጁ ሆነው፣ ከመማርያ ክፍል ጉብኝት እስከ አጠቃላይ የት/ቤት ስብሰባ የሚያካትት ነው። አርበኛ ከሆንክና ወደ ትምህርት ቤት አርበኛ ይዛችሁ ሂዱ ቀን ክውነት ለመሳተፍ ፍላጎት ካለህ፣ የልጅህን ት/ቤት (ወይም በማህበረሰብህ የሚገኝ ትም/ቤት) ክውነት ያስተናግዱ እንደሆነ መጠየቅ ትችላለህ።

5th Annual Choose Respect Conference (5ኛው የማክበር ምርጫ ስብሰባ) ቀን ቆጥቡ!

ቀን መቁጠሪያችሁን ምልክት አድርጉባቸው! 5ኛው Choose Respect Healthy Teen Dating Conference (ጤነኛ የወጣት ቀጠሮ የማክበር ምርጫ ስብሰባ) ፌብሩዋሪ 23 2014 ታኮማ ፓርክ በሚገኘው የMontgomery College ባህላዊ ስነጥበብ ማእከል ይከናወናል። ወጣቶች፣ ወላጆች እና የወጣት አገልግሎት አቅራቢዎች በዚህ ነፃ ክውነት እንዲገኙ ተጋብዘዋል። ተሳታፊዎች በጨዋታ፣ በህብረገቢር እና በትምህርታዊ ዎርክሾፖች የመሳተፍ እድል ይኖራቸዋል። ሎተሪዎች፣ ሽልማቶች፣ ነፃ ምግብ እና መዝናኛዎችም ይኖራሉ

ከ8 – 12 ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎች Healthy Teen Dating Public Service Announcement (ጤናማ የወጣት ቀጥሮ ህዝባዊ አገልግሎት ማስታወቂያ) (PSA) ውድድር በቀጠሮ በደል እና በቤተሰብ ሁከት ያተኮረ ባለ 60-ድቂቃ ኦሪጂናል ቪድዮ በማቅረብ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ። ሶስቱ ከፍተኛ ቪድዮዎች የጥሬ ገንዘብ ሽልማት ይቀበላሉ። አሸናፊዎቹ በስብሰባው ወቅት ይነገራሉ።

ስለ ስብሰባው ወይም ስለPSA ውድድር ተጫማሪ መረጃ፣ በ240-777-7075 ደውሉ ወይም ለTom Manion (ቶም ማንዮን) በThomas.manion@montgomerycountymd.gov ኢሜይል አድርጉ።